የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መሰረተ እምነት

ኢትዮጵያ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ አምልኮተ እግዚአብሔር ሲፈፀምባት የኖረች ጥንታዊት ሃገር ነች። በዘመነ-ሐዲስም ክርስትናን በመቀበል ቀደምት ናት።

መጽሐፍ ቅዱስና ታሪካዊ ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ኢትዮጵያ በሐዋርያት ዘመን ጥምቀተ ክርስትናን በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካይነት ተቀብላለች (የሐዋ 8÷26-36)። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) በመጽሐፍ ቅዱስ እና በሱም ላይ በተመሰረቱት በሶስቱ ዓለም አቀፍ ጉባዔዎች በኒቅያ (325 ዓ.ም.)፤ በቁስጥንጥንያ (481 ዓ.ም.) እና በኤፌሶን (431 ዓ.ም.) በተደነገጉት የሃይማኖት መግለጫዎች ላይ የተገነባ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ዋና ዋናዎቹን የቤተክርስቲያናችንን መሠረተ እምነት መግለጫዎች በአጭሩ እናያለን።

የእግዚአብሔር መኖር

የማይታይና የማይመረመር ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉን የፈጠረ መጀመሪያ ያልነበረው መጨረሻም የማይኖረው ለዘላለም የሚኖር አንድ አምላክ እግዚአብሔር መኖሩን እናምናለን።እርሱም ዘላለማዊ እና ሁሉን ቻይ አምላክ ነው፤ ሁሉን ዐዋቂ እና በዓለም ሁሉ ምሉዕ ነው፤ ቅዱስ# ጻድቅ እና ፍቅር ነው።

ምሥጢረ-ሥላሴ

እግዚአብሔር በባሕርይ# በመለኮት# በፈቃድ# በሥልጣን አንድ ነው። ግን በስም# በአካልና በግብር ሦስትነት አለው።

የስም ሦስትነት፦ አብ#ወልድ#መንፈስቅዱስ።

የአካል ሦስትነት፦ አብ ፍፁም አካል አለው፤ ወልድ ፍፁም አካል አለው፤ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ፍፁም አካል አለው።

የግብር ሦስትነት፦ አብ ወላዲና አስራጊ ነው። ወልድ ተወላዲ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሠራጊ ነው። በሦስቱ አካላት መቀዳደምና መበላለጥ ግን የለም።

ሥነ-ፍጥረት

ይህ የሚታየው ዓለምና በውስጡ ያለው ሁሉ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው። ከዚህ ከሚታየው ዓለም ውጪም ሌላ የማይታይ ረቂቅ ዓለም በውስጡም ያሉት ረቂቃን ፍጥረታት አስቀድሞ ከነበረ ግብር ሳይሆን እምነበ አልቦ በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል። የፍጥረታት ዓላማ እግዚአብሔርን ማመስገን ሲሆን በተለይ ሰው ክብሩን ለመውረስ የተፈጠረ ነው። የተለያዩ ፍጥረታት (ብዛታቸው 22) በስድስት ቀናት ተፈጥረዋል።

የእግዚአብሔር መግቦት

ዓለም በእግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር ከመጣበት ዕለትና ሰዓት ጀምሮ በእግዚአብሔር መጋቢነት ሲመገብ በእግዚአብሔር ጠባቂነት ሲጠበቅ ይኖራል። እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረው ጀምሮ ለዐይን ቅፅበት እንኳ ተለይቶት አያውቅም። በልዩ ጥበቃ ይጠብቀዋል፤ ይከባከበዋል፤ እንዲሁም ይመግበዋል።

መላእክት

መላእክት በማይታየው ረቂቁ ዓለም የሚኖሩ ሲሆን ተፈጠሮአቸውም ከነፋስና ከእሳት ነው። ቁጠራቸው የማይወሰን እጅግ ብዙ ሲሆን ሥራቸውም ተልዕኮ ነው። ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች ለምሕረትም ለመዓትም ይላካሉ (ሉቃ 1÷19-26) ፤ ባለማቋረጥ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፤ የቅዱሳንን ፀሎት ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ (ራዕ 8÷3-4) ፤ በችግር ጊዜ ይራዳሉ (የሐዋ 5÷19፤ 12÷7) ፤ በፍርድ ቀን ከጌታ ጋር ይመጣሉ። በጠቅላላው በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል መልእክተኞች ሆነው ተልዕኳቸውን ይፈፅማሉ።

ሰይጣናት

መላእክት ሁላቸው መልካም ተፈጥሮታቸውን አልጠበቁም። ከእነርሱ አንዱ ዲያብሎስ በነፃ ፈቃዱ ወደ ክፋት አዘንብሎ በትዕቢቱ ወደ ሰይጣንነት ተለውጧል፤ በዘላለማዊ ፍርድም ወደ ጨለማ ተጥሏል። ሰይጣን ሁል ጊዜ ሰዎችን ይፈትናል፤ ወደ ክፉ ይመራል፤ የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲተላለፉ ያደርጋል።

የሰውተፈጥሮናአወዳደቁ

በዚህ በሚታየው ግዙፍ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ እጅግ የከበረና የፍጥረት ሁሉ አክሊል የሆነ ሰው ብቻ ነው፤ ሰው ሲባል ነፍስና ሥጋ ያሉት ፍጡር ነው።ሰው ረቂቅ ነፍስ ብትኖረውም መልአክ አይደለም፤ ግዙፍ አካል ቢኖረውም እንስሳ አይደለም፤ ከመልአክም ከእንስሳም የተለየ ነው። ሥጋዊና መዋቲ በመሆኑ ከመላእክት ይለያል፤ ነባቢት#ለባዊትና ሕያዊት ነፍስ ያለችው በመሆኑ ደግሞ ከእንስሳት ይለያል። የሰው ተፈጥሮ “ለይኩን” በሚል ቃል ሳይሆን በእግዚአብሔር እጅ በርሱ አርአያና ምሳሌ ነፃ ፈቃድ ያለው ሆኖ ተፈጥሯል። ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም ስላይደለ እግዚአብሔር ከአዳም ጎን ሔዋንን ፈጠረለት፤ የሰው ዘር ሁሉ ከነዚህ ከሁለቱ ከአዳምና ሔዋን ተገኝቷል።

ሰው በተፈጥሮው ነፃ ፈቃድ ያለው ፍጥረት በመሆኑ በነፃ ፈቃዱ አመዛዝኖ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰይጣን መታዘዝን መረጠ። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፈ፤ ይህም ኃጢአት ለዘሩ ሁሉ ተላለፈ። በኃጢአት ከወደቀና ከተረገመ ለሰይጣንም ተገዥ ከሆነ በኋላ ወልዷቸዋልና ልጆቹ ሁሉ እንደርሱ ኃጢአተኞች ሆነዋል

(ዘፍ 5÷3)። ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ከገነት ወጣ፤ ልጅነቱን አጣ፤ ፀጋው ተገፈፈ። የፈጣሪውን ትዕዛዝ በመተላለፉ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ፤ ርደተ-መቃብርና ርደተ-ገሃነም ተፈረደበት (ዘፍ 3÷19፤ሮሜ 6÷23) ።

መሥጢረ-ሥጋዌ

ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመተላለፍ ፀጋው ተገፎ ከገነት ወጥቷል። ይሁን እንጂ በተፈጥሮ የተሰጠው ዕውቀቱና ነፃ ፈቃዱ ስላልተለየው እግዚአብሔር በፈታሒነቱ ቢፈርድበትም በመሐሪነቱ እንደሚምረው ስላወቀ በኃጢአቱ ተፀፀተ። እግዚአብሔርም ንስሐውን ተቀብሎ ከሰይጣን ባርነት ከኃጢአት ቁራኝነት ነፃ ያወጣው ዘንድ ፈቀደ። ስለዚህም የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ ከሶስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ በፍፁም አካላዊና ባሕርያዊ ተዋህዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን# ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ ሰው ሆኖ ተወለደ። ተወልዶም ከኃጢአት በቀር የሰውነትን ሥራ ሁሉ እየሠራ አደገ፤ በሰላሳ ዓመቱ ተጠመቀ፤ በጸንጠናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ታመመ፤ ሞተ፤ ተቀበረ፤ በሶስተኛውም ቀን ተነሣ፤ በ 40 ኛው ቀን ወደ ባሕርይ አባቱ በክብር አረገ፤ በተነሣ በ 50 ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ለደቀመዛሙርቱ ላከላቸው።

ቃለ-እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምናለን። የመጀመሪያው ቅድመ-ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደው ሲሆን ሁለተኛው ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ያለአባት የተወለደው ልደት ነው። አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ ሰውም በተዋሕዶ አምላክ ሆነ። የቃል ገንዘብ ለሥጋ# የሥጋም ገንዘብ ለቃል ሆነ። የቃል ገንዘብ ማለት አምላክነት የባሕርይ# ምስጋና# ቀዳማዊነት# ገቢረ-ተዓምራት# ሕያውነት ለሥጋ ገንዘቡ ሆነዋል።እንደዚሁም የሥጋ ገንዘብ ማለት ትሕትና# ድካም# መራብ# መጠማት# ሕማም# ሞት እና ሌሎችም ለቃል ገንዘቡ ሆነዋል። እንደዚሁም ቅድመ-ዓለም ከአብ የተወለደው ቃለ-እግዚአብሔር ወልድ ድኅረ-ዓለም በሥጋ ወልደ ማርያም መባልን ገንዘብ አደረገ። ድኅረ-ዓለም ከእመቤታችን የተገኘው ሥጋም በቃል ወልደ አብ መባልን ገንዘብ አደረገ። ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋህዶ ከበረ።

የክርስቶስ ሕማም# ሞት# ትንሣኤና ዕርገት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣቱ ስለ ዓለም ቤዛ በመስቀል ላይ ተሰቅሎና ሞቶ ዓለምን ለማዳን ነው። ሞቱ ለበደላችን ሁሉ ካሳ (ቤዛ) ነው (ማቴ 20÷28)። ሞቱ ሞትን ደምስሶልናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ በሶስተኛው ቀን በመለኮታዊ ሥልጣኑ ተነስቷል። በክርስቶስ ትንሣኤ ሞትና ሰይጣን ድል ሆነዋል (1 ቆሮ 15÷16፡ 20፤ሮሜ 6÷3-11፤ኤፌ 2÷4-6)፤ የሰው ልጅ ድኅነት ተፈፅሟል (ሮሜ 4፤25)፤ የርሱ ትንሣኤ የኛን ትንሣኤ ያረጋግጥልናል፤ እርሱ በክብር እንደተነሣ እኛም እንደሱ በክብር እንነሳለን (1 ቆሮ 15÷20-22)። ትንሣኤው ለክርስትና እምነት መሠረት ነው (1 ቆሮ 15÷17-18)። ጌታችን ከተነሳ በኋላ በአርባኛው ቀን በክብር ወደ ሰማይ አረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ይህም የአድኅኖቱ ሥራ ፍፃሜ ነው።

ድንግልማርያምወለዲተአምላክ

ድንግል ማርያም ከቤተ-ዳዊት የተወለደች ናት። በ 15 ዓመት እድሜዋ በብሥራተ-መልአክ በግብረ-መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወለደች። ቅድስት ማርያም ዘላለማዊት ድንግል ናት፤ ከመፅነስ በፊት# በመፅነስ ጊዜ እና ከመፅነስ በኋላም ድንግል ናት። ከመውለድ በፊት# በመውለድ ጊዜ እና ከመውለድ በኋላም ድንግል ናት። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሐሳብም# በቃልም በግብርም ኃጢአት የሌለባት ፍፅምት ንፅሕት ናት። ይሁን እንጂ እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችም፤ ካሳ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት። ንፅሕት ቅድስት ማርያም ክብር ምስጋና የሚገባት ናት። መላእክትም ሰዎችም አክብረዋታል አመስግነዋታል (ሉቃ 1÷28-29፤ሉቃ 1÷40-42) ። ድንግል ማርያም እመ-አምላክ ወይም ወላዲተ-አምላክ ተብላ ትጠራለች (ሉቃ 1÷32) ። እርስዋ በእግዚአብሔር ዘንድ ከፍተኛ ባለሙዋል ስለሆነች አማላጃችን ናት፤ እርስዋ ለእኛ የአደራ እናታችን ናት፤ እኛም ለእርሷ የአደራ ልጆች ነን (ዮሐ 19÷27-29) ስለዚህ ትማልድልናለች። እመቤታችን በ 64 ዓመት እድሜዋ አዳማዊ ሞትን ሞታለች፤ ይሁን እንጂ ሙስና መቃብር አላገኛትም፤ በሞተች በሶስተኛው ቀን በእግዚአብሔር ኃይል ተነስታ በክብር አርጋለች።

ትንሣኤ ሙታን# የክርስቶስ ዳግም ምፅአትና የመጨረሻው ፍርድ

የዚህ ዓለም ፍፃሜ በሚሆንበት ጊዜ የሙታን ትንሣኤ# የክርስቶስ ዳግም ምፅአት# የመጨረሻው ፍርድና የዘላለም ሕይወት በተከታታይ ይፈፀማሉ። ሞት የሰው ፍፃሜ አይደለም፤ ከጊዜያዊ ሕይወት ወደ ዘላለማዊ ሕይወት መሸጋገሪያ ነው እንጂ። ዛሬ ፈርሶ በስብሶ ዐፈር ሆኖ ያለው የሰው ሥጋ ከነፍስ ጋር ተዋሕዶ ይነሣል። ከትንሳኤ በኋላ ሰዎች ሁሉ እንደ መላእክት ይኖራሉ (ማቴ 22÷30)። ትንሳኤ ሙታን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ይሆናል፤ ከትንሳኤ ሙታን ቀጥሎ ወዲያው ጌታችን ይመጣና የመጨረሻ ፍርድ ይሰጣል፤ ከዚያም የዓለም ፍፃሜ ይሆናል። ቀድሞ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ በትሕትና መጥቶ የነበረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ፍጻሜ ጊዜ ዳግመኛ በክብር ይመጣል። የሚመጣበት ዓመትና ወር# ዕለትና ሰዓት ፈፅሞ አይታወቅም። ዳግመኛ የመምጣቱ ዓላማ “በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ” ይሆናል። በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ጊዜ ሞት ይጠፋል፤ ሰይጣንም ለዘላለም ይታሠራል፤ ሕይወት ብቻ ለዘላለም ይቀጥላል (1 ቆሮ 15÷51-57፤ዕብ 2÷14፤ራዕ 20÷10-15፤ራዕ 22÷12)።

ከላይ የዘረዘርናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ መሠረተ-ሃይማኖት ዋና ዋና መግለጫዎች ቀጥሎ በሰፈረውና ጸሎተ-ሃይማኖት እየተባለ በሚጠራው የእምነት መግለጫ ይጠቃለላሉ።

ጸሎተ-ሃይማኖት

- ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታይና የማይታየውንም በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

- ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን።

- ከብርሃን የተገኘ ብርሃን÷ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ÷ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል#

- ሁሉ በርሱ የሆነ# ያለእርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም፤ በሰማይም ያለ በምድርም ያለ፤ ስለኛ ስለ ሰዎች ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ።

- ሰው ሁኖ በጰንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለኛ ተሰቀለ፤ ታመመ፤ ሞተ፤ ተቀበረም። በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ፤

- በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ። ዳግመኛም ሕያዋንንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

- ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሠረጸ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፤ እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት የተናገረ።

- ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት ባንዲት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያንም እናምናለን።

- ኃጢአትን ለማስተስረይ ባንዲት ጥምቀት እናምናለን።

- የሙታንንም መነሳት ተስፋ እናደርጋለን።

- የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን።

ምሥጢራተ_ቤተክርስቲያን

ምሥጢራተ-ቤተ-ክርስቲያን በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባሉ ሰዎች ብቻ የሚሰጡ# በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ፀጋን# ረቂቅ ሀብትን የሚሰጡ ናቸው።በዚህም የተነሳ ምስጢራት ተብለዋል። ምሥጢራተ-ቤተክርስቲያን በክርስቶስ መሥራችነት የተመሰረቱ፤ ክርስቶስ ራሱ በዕለተ ዓርብ ካደረገው የማዳን ሥራ የመነጨ፤ የማዳን ሥራውም ያለማቋረጥ እስከ ዓለም ጎልፈት እየቀጠለ የሚሄድባቸው፤ ኃይሉ የሚታወቅባቸው ሥልጣኑ የሚገለጥባቸው የማንባትና የማፅናት ሥራው የሚቀጥልባቸው ታላላቅ ምሥጢሮች ናቸው። ምሥጢራተ-ቤተክርስቲያን ቁጥራቸው ሰባት ነው።

እነሱም ምሥጢረ ጥምቀት# ምሥጢረ ሜሮን# ምሥጢረ ቁርባን# ምሥጢረ ንስሐ# ምሥጢረ ክህነት# ምሥጢረ ተክሊል እና ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው።

በአብያተ-ክርስቲያናት መካከል ያሉ የሃይማኖትና የሥርዓት ልዩነቶች

ከዚህ ቀጥሎ በኦርየንታል (በተዋህዶ) ኦርቶዶክስ፤ በግሪክ ኦርቶዶክስ፤ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አብያተ-ክርስቲያናት መካከል ካሉት የሃይማኖትና የሥርዓት ልዩነቶች ጥቂቶቹን እናያለን።

ረዥሙ የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳን በክሕደት ምክንያት ከቤተ-ክርስቲያን አባልነታቸው በጉባዔ ተወግዘው ከተለዩት ከአርዮስ# ከመቅዶንዮስ# ከንስጥሮስ እና ከተከታዮቻቸው በስተቀር እስከኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ በአብያተ-ክርስቲያናት መካከል የእምነት ልዩነት አልነበረም። ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ ግን በዓለም አብያተ-ክርስቲያናት ልዩነቶች ተከስተዋል። ጥቂቶቹን ከዚህ እንደሚከተለው በአጭሩ እናያለን።

- የካቶሊክና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ሲሉ የኦርየንታል (የተዋህዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ነው እንላለን።

- የካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድም ሠረጸ ስትል የኦርየንታል (የተዋህዶ) እና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሠረጸ እንላለን።

- የካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን ብዙ ሰዎች ስለሠሩት ኃጢአት በመፀፀት ንስሐ ገብተው ሳይፈጽሙት ቢሞቱ በመንግስተ-ሰማያትና በገሃነመ-እሳት መካከል ልዩ የሆነ ቦታ (መካነ-ንስሐ/Purgatory) ስላለ ነፍሶቻቸው ወደዚያ ሄደው ከኃጢአታቸው እስኪነጹ ድረስ መከራ እየተቀበሉ ቆይተው ኋላ ወደ መንግስተ-ሰማያት ይገባሉ በማለት የምታስተምረውን ትምህርት የኦርየንታል (የተዋህዶ) እና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት አንቀበለውም።

- የካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን የሮም ፖፕ የክርስቶስ እንደራሴና የአብያተ-ክርስቲያናት ሁሉ በላይ ስለሆነ በመንበሩ ተቀምጦ (ተሰይሞ) በሚወስነው ሁሉ አይሳሳትም ብላ በ 1870 ዓ.ም. በቫቲካን አንድ ጉባኤ የወሰነችውን የኦርየንታል (የተዋህዶ) እና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት አንቀበልም። ይልቁንም

የቤተ-ክርስቲያን መሪዎች በጉባኤ ተሰብስበው በተገኙበት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተወሰነውና ለወደፊትም የሚወሰነው ውሳኔ (ድንጋጌ) ነው የማይሳሳት እንላለን።

• የተዋሀዶ ኦርቶዶክሳውያን የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሃደው ነው ስንል የካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን ግን ነፍስ ያለው መለኮት የተዋሃደው ነው ትላለችእንላለን

• በካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን ሕጻናት ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበሉት ነፍስ ዐውቀው ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ሲሆን በኦርየንታል (የተዋሀዶ) እና በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት ከተጠመቁና ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ወዲያው ይቀርባሉእንላለን

• በ 306 ዓ.ም. በስፔን ሃገር በተደረገችው በኤልቪራ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት የካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን ካህናት በመላ ሚስት አያገቡም። የኦርየንታል (የተዋሀዶ) እና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት ካህናት ግን ከጳጳሳት በስተቀር ቀሳውስትና ዲያቆናት ከፈለጉ አንዳንድ ሚስት አግብተው ሥልጣነ-ክህነት ተቀብለው ሊያገለግሉ ይችላሉ እንላለን።

• በካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን አብዛኛውን ጊዜ ከሥዕል በተጨማሪ ለጌታ ለእመቤታችን ለጻድቃንና ለሰማዕታት መታሰቢያ የድንጋይ ሐውልት ሲቀረፅላቸው በኦርየንታል (የተዋሀዶ) እና በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት ግን አብዛኛውን ጊዜ በሥዕል ይሣላሉ።

• እንዲሁም በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ በሚፈፀሙት የቤተ-ክርስቲያን አገልግሎቶች እና በመሳሰሉት የሁሉም አብያተ-ክርስቲያናት ሥርዓት ይለያያል።

• በ 16 ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ከካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን የተለዩት ፕሮቴስታንቶች የፖፑን የበላይነትና አይሳሳትም የሚለውን ትምህርት አይቀበሉትም።

• የፕሮቴስታንቶች ሃይማኖት መገኛ ስድሳ ስድስቱን መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ እንደመሰለው ሊተረጉመው ይችላል።

•ፕሮቴስታንቶች ምንም እንኳ ማዕርገ ክህነት ለሐዋርያት የተሰጠ ከሐዋርያት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ መሆኑን በመቃወም እንደ ምስጢር ባይቆጠሩትም ከሶስቱ ማዕርገ ክህነት ቅስናንና ዲቁናን ስሙን ብቻ ይቀበላሉ። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ግብረ-ገብነትን የተመረኮዘ መልካም ኑሮ ከኖረና በቂ የመንፈሳዊ ትምህርት ዕውቀት ካለው በአንብሮተ እድ ባይሾምም የካህናትን ሥራ ሊሠራ ይችላል ይላሉ።

• ፕሮቴስታንቶች ከሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ-ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጸጋ የሚሰጥ በጥምቀትና በቁርባን ብቻ ነው ይላሉ። ካህኑ በሚጸልይበት ጊዜ ሕብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ደመ አምላክ አይሆንም ይላሉ። የተወሰኑት የሕጻናትን ጥምቀት ሲቃወሙ የተቀሩት ደግሞ ሕጻናትን አጥምቀው ቅዱስ ቁርባንን የሚሰጧቸው ነፍስ ካወቁ በኋላ ነው። ከፕሮቴስታንቶች ጥቂቶቹ ከመፅሐፍ ቅዱስ በስተቀር ሥርዓታተ ቤተ-ክርስቲያን ፈፅሞ የላቸውም።

• ንስሐን እንደ ምስጢር ሳይቆጥሩ የሰውን ጸባይ ያሻሽላል ሰዎችን ለማፅናናት ይችላል በማለት ቢቀበሉትም ቅሉ ኃጢአትን ለንስሐ አባት መናገር አያስፈልግም ይላሉ።

• ንስሐ ገብቶ ሳይፈጽመው ድንገት የሚሞተው ሰው ነፍሱ በንስሐ ቦታ ነፅታ ወደ ወደ መንግስተ-ሰማያት ትገባለች የሚለውን የካቶሊኮችን እምነት አይቀበሉትም።

• ለጌታ ሁለት ባሕርያት አሉት መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሠረጸ ብለው ያምናሉ።

• ምንኩስናን ማዕርገ ክህነትን የጻድቃንን ማማለድ አይቀበሉም። የጻድቃንና የሰማዕታት ሥዕሎች በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ መገኘትን ለነሱም የፀጋና የአክብሮት ስግደት ማድረግን አይቀበሉም።

• የኦርየንታል (የተዋህዶ) የግሪክ ኦርቶዶክስ እና የካቶሊክ አብያተ-ክርስቲያናት ቁሱ በሚፀልይበት ጊዜ ጎብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ደመ አምላክ ይሆናል ሲሉ ፕሮቴስታንቶች አይለወጥም ብለው ያምናሉ።

• የኦርየንታል (የተዋህዶ) የግሪክ ኦርቶዶክስ እና የካቶሊክ አብያተ-ክርስቲያናት ድኅነት የሚገኘው ከእምነትና ከደጋግ ሥራዎች ነው ሲሉ (ያዕ 2÷14-26፤ማቴ 7÷21) ፕሮቴስታንቶች ግን ድኅነት የሚገኘው ከእምነትና ብቻ ነው ይላሉ።

ፕሮቴስታንቶችን በሚመለከት ከዚህ በላይ ባጭሩ የተዘረዘሩት እምነት ነክ ትምህርቶች ቀደምትና ዋናዋና በሆኑት የፕሮቴስታንት አብያተ-ክርስቲያናት የሚሰጡ ትምህርቶች ናቸው እንጂ የሁሉንም አያጠቃልሉም።

ይቀጥላል...

ስብሐት ለእግዚአብሔር# ወለወላዲቱ ድንግል# ወለመስቀሉ ክቡር!!!
ይቆየን።

ምንጭ

1. ሉሌ መላኩ (1986) የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ። ትንሳዔ ማሳተሚያ ድርጅት፤ አዲስአበባ (ገጽ 56-60)።
2. ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ (1982) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት ተልዕኮ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፤ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ፤ አዲስአባባ።
3. አባ ጎርጎርዮስ ካልዓይ (1993) ሰባቱም ሥጢራተ-ቤተክርስቲያን። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጀ መምሪያ፤ ማኅበረ-ቅዱሳን፤ አዲስአበባ።
4. አባ ሀብተ-ማርያም ወርቅነህ (n.d.) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን እምነትና ትምህርት። ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፤ አዲስአበባ።
5. www.eotcmk.org

To download

EOTC preaching in English

Sunday On EBS Wereb for Gena beal